

# የትምህርት ዓመቱን መጀመር

## የሁለተኛ ደረጃ የርቀት ትምህርት የወላጆች መመሪያ

Arlington Public Schools

# የኃላፊው መልዕክት

**ወድ የአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ወላጆች፣**

በወረርሽኝ ምክንያት፣ አርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የ2020-21 የትምህርት ዘመኑን በሙሉ ሰዓት በርቀት ትምህርት ይጀምራል፣ የሚጀምረው ማክሰኞ ሴፕቴምበር 8 ቀን ነው። ሁሉንም ተማሪዎች እንኳን በድጋሚ ወደ ትምህርት ቤት መጣችሁ እንላለን፤ በእኛ በኩል ተማሪዎች በአካል ተገኝተው ትምህርት ለመከታተል ሁኔታዎች የሚፈቅዱበትን ጊዜ ለመወሰን የኮቪድ-19 ወቅታዊ ሁኔታዎችን መከታተላችንን እንቀጥላለን። በአሰራራችን ላይ ለውጦች በሚኖሩ ጊዜ በዌብሳይታችን፣ በኢሜል እና በሌሎች መደበኛ የግንኙነት ዘዴዎች አማካኝነት ከትምህርት ቤቱ መምሪያ እና ትምህርት ቤቶች እናሳውቃችኋለን።

ይህ መመሪያ፣ አዲሱን የትምህርት ዘመን ከርቀት ስንጀምር ስለ ርቀት ትምህርት እንድትገነዘቡ እና ተማሪዎችን ለማገዝ ይረዳል። ስለ ትምህርት አሰጣጥ፣ ስለ ማኅበራዊ-የስሜት ትምህርት፣ ተማሪዎች የሚጠብቁትን፣ በትምህርት መገኘት/መቅረት፣ የቴክኒክ ድጋፍ እና ሌሎችንም መረጃዎች ታገኛላችሁ። ሁሉም ተማሪዎች በየትኛው የአስተማመር ዘዴ ቢሆን ጥራቱን የጠበቀ የትምህርት ልምድ እንዲኖራቸው ለማድረግ ቁርጠኛ አቋም አለን። ሁሉም ተማሪዎች ለመማር እና ለማደግ የሚያስፈልጋቸው አካዳሚያዊ እና ማኅበራዊ-የስሜት ኃብቶች እና ድጋፍ ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ እንሰራለን።

የAPS መሪዎች የጤና ሁኔታዎችን መከታተላቸውን ይቀጥላሉ፤ የእኛን የዕቅዶች ለመከለስ ከክፍለ ግዛት እና ከካውንቲ ባለሥልጣኖች ጋር አብረው ይሰራሉ፤ እንደ አስፈላጊነቱም ማስተካከያዎች ያደርጋሉ።

በዚህ አስቸጋሪ ወቅት ለትዕግስታችሁ እና ለአጋርነታችሁ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

ከልብ የእናንተው፣



ዶ/ር ፍራንሲስኮ ዱራን

ኃላፊ

አርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች

## ማውጫ


የትምህርት አሰጣጥ ዕቅድ ምልከታ ..... 4
ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ..... 4
መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ..... 5
የመጀመሪያው ወር - የአጀማመር ምክሮች ..... 6
ኦገስት 31 - ሴፕቴምበር 4፡- ከትምህርት ቤት መግቢያ በፊት ያለው ሳምንት ..... 6
የመጀመሪያ የትምህርት ቀን፡- ሴፕቴምበር 8 ..... 7
የመጀመሪያ ወር ..... 8
ሲንክራኒየስ እና አሲንክራኒየስ የትምህርት ጊዜ ..... 9
ሲንክራኒየስ ..... 9
ትምህርቶችን ስለመቅዳት ..... 9
አሲንክራኒየስ ..... 9
የቤት ሥራ ..... 10
ከተማሪዎች የሚጠበቁ ነገሮች ..... 11
አማራጮ ትምህርቶች (ጤና እና የአካል ብቃት ትምህርት፣ ስዕል እና CTE) ..... 12
የማኅበራዊ-የሥሜት ትምህርት (SEL) እና ድጋፍ ..... 13
የልዩ ትምህርት ተማሪዎች ልዩ አገልግቶች ..... 14
ልዩ አገልግሎቶች ለእንግሊዝኛ ተማሪዎች ..... 15
በባለ ልዩ ችሎታ ተማሪዎች የሚሰጡ ልዩ አገልግሎቶች ..... 16
ከትምህርት ቤት ሰዓት በኋላ የሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች እና ስፖርት ..... 17
አትሌቲክስ ..... 17
ክለቦች እና እንቅስቃሴዎች ..... 17
በትምህርት ቤት መገኘት ..... 18
የዕለት ተዕለት በትምህርት ገበያ መገኘት ..... 18
ምዘና እና ውጤት ..... 19
የቴክኖሎጂ ድጋፍ ..... 19
የወላጆች አካዳሚ ..... 20
የእርስዎን ተማሪ መደገፍ ..... 20
ጤና እና ደህንነት፡- ወደ ሃይብሪድ ሞዴል መሸጋገር ..... 21
ቁልፍ ተወካዮች ..... 21

## የትምህርት አሰጣጥ ዕቅድ ምልከታ

በሁሉም የክፍል ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎች በሲንክራኒየስ (ቀጥታ-ኦንላይን) እና በአሲንክራኒየስ (ራስን ችሎ-ኦንላይን ወይም ኦፍስክሪን) ትምህርት በሳምንት ለ4 ቀናት፣ ከማክሰኞ እስከ ዓርብ ይማራሉ፡፡ ተማሪዎች በፌብርዋሪ 2020 በመረጧቸው ትምህርቶች ላይ ይሳተፋሉ፡፡

በሰኞ ቀናት ተማሪዎች በአሲንክራኒየስ ትምህርት የሚሳተፉ ሲሆኑ፣ መምህራን ደግሞ በትብብር ዕቅድ ማውጣት እና በአነስተኛ ቡድኖች እገዛ ከአንዳንድ ተማሪዎች ጋር እንደ አስፈላጊነቱ በሲንክራኒየስ ዘዴ ይሳተፋሉ፡፡

### ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን የአካዳሚ ፍላጎቶች ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ እንደ ቀድሞ ዓመታት ሁሉ ለእያንዳንዱ ትምህርት መምህራን ይመደቡላቸዋል፡፡ አንዳንድ ተማሪዎች እንደ ምርጫቸው በአካል ተገኝተው ትምህርት ወደሚያገኙበት የማስተማር ዘዴ ሲሸጋገሩ፣ ሁሉም የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የትኛውንም ሞዴል ቢመርጡ በተመሳሳይ መምህር እንዲማሩ ይደረጋል፡፡ ይህም ማለት አንድ ተማሪ በአካል በመገኘት ትምህርት ወደሚሰጥበት የአስተማመር ዘዴ ሲዘዋወር/ ስትዘዋወር ለአንዳንድ የትምህርት ዓይነቶች መምህሩ በክፍል ውስጥ ተገኝተው ማስተማር በማይችሉበት ሁኔታ በቀጥታ ሊማር ይችላል ማለት ነው፡፡ እነዚህ ያሉትም ክፍሎች ትምህርቱ በርቀት በመሰጠት ላይ ሳለ በሌላ ሠራተኛ ክትትል ይደረጋል ማለት ነው፡፡

በ APS መምህር በሚሰጥ ትምህርት ላይ ለመሳተፍ ካልተቻለ፣ ተማሪዎች በኦንላይን አስተማሪ በሚሰጥ ትምህርት ለምሳሌ በቨርቹዋል ቨርጂኒያ በሚሰጥ ትምህርት ላይ መሳተፍ ይችላሉ ማለት ነው፡፡

#### የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ናሙና የጊዜ ሰሌዳ

<table>
<tr><th>ሰኞ ቀናት</th><th>ከማክሰኞ - ዓርብ<br>(ሲንክራኒየስ እና አሲንክራኒየስ፣ ሁሉም ክፍሎች፣<br>በቀን 5 ሰዓት ከ35 ደቂቃ)</th></tr>
<tr><td rowspan="7"><ul><li>መልዕክት፡-<br>በአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎች በትምህርት ቤቱ ሠራተኞች በሚመራ አሲንክራኒየስ የመልዕክት አቅርቦት ላይ ይሳተፋሉ፡፡</li><li>የመምህራን ዕቅድ አወጣጥ</li><li>የትብብር ቡድን (CLT)፣ የክፍል ደረጃ ወይም ሌላ የተማሪዎች ስብሰባዎች</li><li>መምህራን/አማከሪ ቢሮ ሰዓታት</li><li>የምሪት አነስተኛ ቡድን እና የአንድ ለአንድ አገልግሎት</li><li>ተማሪዎች በአሲንክራኒየስ ትምህርት ውስጥ ይሳተፋሉ (በእያንዳንዱ ትምህርት በግምት 30 ደቂቃ)</li><li>አሲንክራኒየስ SEL ትምህርት</li></ul></td><td>1ኛ ወይም 2ኛ ጊዜ (በድምሩ 89 ደቂቃ፤ 50 ደቂቃ አሲንክራኒየስ)</td></tr>
<tr><td>የሽግግር ጊዜ (5 ደቂቃ)</td></tr>
<tr><td>3ኛ ጊዜ (በድምሩ 50 ደቂቃ፤ 30 ደቂቃ ሲንክራኒየስ)</td></tr>
<tr><td>ምሣ (60 ደቂቃ)</td></tr>
<tr><td>4ኛ ወይም 5ኛ ጊዜ (በድምሩ 95 ደቂቃ፤ 50 ደቂቃ አሲንክራኒየስ)</td></tr>
<tr><td>የሽግግር ጊዜ (5 ደቂቃ)</td></tr>
<tr><td>6ኛ ወይም 7ኛ ወቅት (በድምሩ 95 ደቂቃ፤ 50 ደቂቃ አሲንክራኒየስ)</td></tr>
</table>

## መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

### ናሙና የጊዜ ሰሌዳ

| ሰኞ ቀናት | ከማክሰኞ - ዓርብ<br>(ሲንክራኒየስ እና አሲንክራኒየስ፣ ሁሉም የክፍል ደረጃዎች<br>በቀን 5 ሰዓት፣ ከ43 ደቂቃ) |
|---|---|
| • የመምህራን ዕቅድ አወጣጥ<br>• የትብብር ቡድን (CLT)፣ የክፍል ደረጃ ወይም ሌሎች የተማሪዎች ግንኙነቶች<br>• መምህራን/አማካሪ ቢሮ ሰዓታት<br>• የምሪት አነስተኛ ቡድን እና የአንድ ለአንድ አገልግሎት<br>• ተማሪዎች በአሲንክራኒየስ ትምህርት ውስጥ ይሳተፋሉ (በእያንዳንዱ ትምህርት በግምት 30 ደቂቃ)<br>• አሲንክራኒየስ SEL ትምህርት | 1ኛ ወይም 2ኛ ጊዜ (በድምሩ 89 ደቂቃ፤ 50 ደቂቃ አሲንክራኒየስ) |
| | የሽግግር ጊዜ (5 ደቂቃ) |
| | 3ኛ ወይም 4ኛ ጊዜ (በድምሩ 87 ደቂቃ፤ 50 ደቂቃ አሲንክራኒየስ) |
| | 5ኛ ጊዜ (45 ደቂቃ፤  30 ደቂቃ ሲንክራኒየስ)<br>የመምህር ምክር (TA) (በድምሩ 35 ደቂቃ) |
| | ምሣ (50 ደቂቃ) |
| | የሽግግር ጊዜ (4 ደቂቃ) |
| | 6ኛ ወይም 7ኛ ጊዜ (በድምሩ 87 ደቂቃ፤ 50 ደቂቃ ሲንክራኒየስ) |

# የመጀመሪያው ወር - የአጀማመር ምክሮች

## ኦገስት 31 - ሴፕቴምበር 4፡- ከትምህርት ቤት መግቢያ በፊት ያለው ሳምንት

የርቀት ትምህርት ለተማሪዎች እና ለቤተሰቦቻቸው አዲስ ነው፤ አዲሱን የጊዜ ሰሌዳ እና ፎርማት ለመላመድ ደግሞ ጊዜ ያስፈልጋል። ተማሪዎን ለርቀት ትምህርት ዝገጁ ለማድረግ ከዚህ የሚከተሉትን ጥቂት እርምጃዎች ሊወስዱ ይችላሉ፡-

### በቤት ውስጥ

- የሚቻል ከሆነ ለልጅዎ መማሪያ ስፍራ ያዘጋጁ። ለዚህ ምቹ ይሆናል የሚባለው ስፍራ ጸጥታ ያለው ሆኖ ተማሪዎ የመማሪያ መገልገያውን እና ማቴሪያሉን መዘርጋት የሚችልበት/የምትችልበት ጠረጴዛ ወይም ዴስክ ያለበት ነው።
- በኦንላይን ክፍለ ጊዜ በተለይም በርካታ ወንድሞች/እህቶች ካሉ እና ሌሎች የሚረብሹ ነገሮች ካሉ ልጅዎ ሄድፎን እንዲጠቀም/እንድትጠቀም ያድርጉ።
- የዕለት ተዕለት ተግባራትን መፈጸም ጀምሩ፡-
    - የትምህርት ክፍለ ጊዜ ከመጀመሩ በፊት ቁርስ ለመመገብ እና ለመልበስ በጠዋት መነሳት።
    - ስለ ምሣ ጊዜ አስቀድማችሁ አስቡ፤ የ APS የምግብ አገልግሎቶች የምትጠቀሙ ከሆነ በቅርብ ያለውን የትምህርት ቤት የምግብ አገልግሎት ለመጠቀም አስቡ፤ በሰኞ፣ ረቡዕ እና ዓርብ ቀናት ምግብ ይዛችሁ ለመምጣት ዕቅድ ያዙ።
        - የመጀመሪያ ደረጃ እና የመለስተኛ ደረጃ ተማሪዎች በእያንዳንዱ ቀን የ50 ደቂቃ የምሣ ሰዓት አላቸው፤
        - የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ደግሞ በእያንዳንዱ ቀን የ60 ዲቂቃ የምሣ ሰዓት አላቸው።
    - ከትምህርት ጊዜ በኋላ ላለ አካላዊ እንቅስቃሴ፣ ለዕረፍት ጊዜ፣ የዕረፍት ጊዜ ማሳለፊያ ተግባራትን ለማከናወን ወዘተ
    - በእያንዳንዱ ከሰዓት ጊዜ ልጅዎን ለማየት ዕቅድ ያዙ።
        - በዛሬው ዕለት ምን ተማርክ/ሽ?
        - በዛሬው ዕለት ምን ዓይነት ተግዳሮት ገጠመህ/ሽ እና ነገ የተሻለ እንዲሆን ምን ማድረግ እንችላለን?
    - የአዕምሮን ጤና ለመደገፍ ጤናማ ራት ተመገቡ።
    - በቂ እንቅልፍ ለማግኘት በመደበኛ ሰዓት ወደ እንቅልፍ ሂዱ።

### ለትምህርት ዝግጁ መሆን

ትምህርት ከመጀመሩ በፊት የልጅዎ ትምህርት ቤት የጊዜ ሰሌዳ እና የቲምስ፣ የካንቫስ ወዘተ በማዘጋጀት ይጠብቅዎታል። የልጅዎ ትምህርት ቤት ወይም መምህር ከእርስዎ ጋር ካልተገናኘ ለዋናው መሥሪያ ቤት ይደውሉ።

በርካታ ትምህርት ቤቶች በዚህ ሳምንት ቨርቹዋል ኦፐን ሃውስ እና ወደ ትምህርት ቤት የመመለስ ዝግጅቶች አሏቸው፤ የጊዜ ሰሌዳውን ለማግኘት እባክዎን የትምህርት ቤቱን ዌብሳይት ይመልከቱ ወይም ለዋናው መሥሪያ ቤት ይደውሉ።

- መጀመሪያ እና ማጠናቀቂያ ሰዓታትን፣ የምሳ እና የትምህርት ክፍለ ጊዜያትን በማካተት የልጅዎን የጊዜ ሰሌዳ ይመልከቱ። ይህንን ፕሪንት ማድረግ እና በልጅዎ የመማሪያ ስፍራ አቅራቢያ መለጠፍ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።
- ትምህርት የሚጀምርበትን ጊዜ እና የትምህርት ክፍለ ጊዜው ምን እንደሚሆን ካላወቁ፣ በዚህ ሳምንት ትምህርት ቤታችሁን ያነጋግሩ።

    - መደበኛ የሥራ ሰዓት መጀመሪያ እና ማጠናቀቂያ በ APS ዌብሳይት ተለጥፈዋል (apsva.us/school-year-2020-21/school-start-end-times/)።
    - እንዲሁም ወደ StudentVUE በመግባት የተማሪዎን የጊዜ ሰሌዳ መመልከት ይችላሉ።
- የልጅዎን የትምህርት መገልገያዎች ስለመቀበል እና ስለ ትምህርት ማቴሪያሎች ከልጅዎ ትምህርት ቤት መረጃዎችን ይውሰዱ።
- ተማሪዎ የ APS የትምህርት ማቴሪያሎች (አይፓድ ወይም ማክቢክ ኤር) እንዳለው/እንዳላት እና መሣሪያው እንደሚሰራ እና ሎግ ኦን ማድረግ እንደሚቻል ያረጋግጡ።
    - የ APS የትምህርት መገልገያ ካልደረሳችሁ ወይም ሎግ ኦን  ማድረግ ካስቸገራችሁ ትምህርት ቤታችሁን አነጋግሩ።
- ከልጅዎ ጋር ወደ አፕሊኬሽኖች ሎግ ኢን ለማድረግ ተለማመዱ።
    - የሚፈለጉት አፕሊኬሽኖች ሁሉ በመገልገያው ላይ መኖር አለባቸው።
    - የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት፡- ሲሳው፣ ካንቫስ፣ ጉግል ክላስሩም፣ ማይክሮሶፍት ቲምስ፣
    - ሁለተኛ ደረጃ፡- ካንቫስ፣ ማይክሮሶፍት ቲምስ

- የልጅዎን የ APS የተማሪ መለያ ቁጥር እና ፓስወርድ እወቁ፤ ይህ መረጃ ልዩ ልዩ አፕሊኬሽኖችን ለማግኘት ይረዳችኋል።
- በመገልገያው ላይ ያለውን ማይክሮፎን እና ካሜራ መሥራቱን ያረጋግጡ፤ ሄድፎን ካለ ደግሞ የሚሰራ መሆኑን እርግጠኛ ሁኑ።

## የመጀመሪያ የትምህርት ቀን፡- ሴፕቴምበር 8

- ከአንድ ምሽት በፊት መገልገያችሁን ሙሉ በሙሉ ቻርጅ አድርጉ።
- ልጅዎን በጠዋት በማስነሳት ቁርስ እንዲበላ/እንድትበላ እና እንዲለብስ/እንድትለብስ ያድርጉ።
- የትምህርት ክፍለ ጊዜ በትምህርት ቤቱ መደበኛ የትምህርት መጀመሪያ ሰዓት ይጀምራል፤ ከልጅዎ መምህር የተቀበሉትን የትምህርት ክፍለ ጊዜ ይመልከቱ።
- ትምህርት መጀመሩ ቢያንስ ከ5 ደቂቃ በፊት ልጅዎ ወደ መገልገያው እንዲገባ እና ወደ ማይክሮሶፍት እንዲገባ ወይም ሎግ ኢን እንዲያደርግ ያድርጉ።
- የመገናኘት ችግር ካለ፣ ለምክሮች እና ኃብቶች፣
- የመገናኘት ችግር ካለ፣ ምክሮች እና አገልግሎቶች የቴክኖሎጂ ክፍሉን ይመልከቱ።
    - ልጅዎ ቀሪ ተብሎ/ላ እንዳይመዘገብ/እንዳትመዘገብ እባክዎን ከ5:00 ፊት ትምህርት ቤቱን አግኙ።

- ልጅዎ ክፍሎች፣ መታጠቢያ፣ ዕረፍት ወዘተ መካከል መንቀሳቀስ እንዲችል/እንድትችል ለማድረግ በተቻለ መጠን በመጀመሪያ ቀን በክፍል ውስጥ ይገኙ። ይህም በልምምድ እየቀለለ ይሄዳል!

## የመጀመሪያ ወር

በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ሳምንታት ውስጥ መምህራን እና ተማሪዎች አዳዲስ የእለት ተዕለት ተግባራት ለማከናወን እና ለትምህርት መሠረት በመሆን መልኩ ጠንካራ ማኅበረሰብ ለመመስረት እንዲያስችላቸው ተደርገው የተነደፉ ናቸው። ተማሪዎች በልዩ ሁኔታዎቻቸው እና የመላመድ አቅም ላይ በመመስረት ከአዳዲስ ቴክኖሎጂ ጋር ይላመዳሉ። ተማሪዎች በቨርቹዋል የትምህርት ክፍል ውስጥ የሚጠብቋቸው ነገሮች ላይ ለውጥ ለማድረግ እና ጥያቄ ለመጠየቅ እንዲችሉ ጊዜ ይሰጧቸዋል፤ እንዲሁም በሂደት የዋናው ሥርዓተ ትምህርት አካል በሆነ መልኩ አዳዲስ ይዘት እንዲያስገቡ ያግዟቸዋል።

መነሻው ቅድሚያ የምንሰጠው ጉዳይ ማኅበረሰብን መገንባት፣ የተማሪዎችን ማኅበራዊ-የስሜት ፍላጎቶች ማሟላት እና ለትምህርት ዝግጁ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው። በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ሳምንታት ውስጥ አንዳንድ ተግዳሮቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ እንገነዘባለን፤ ሆኖም ግን ተማሪዎችን እና ሠራተኞችን በሚቻለው ሁሉ ለመደገፍ ቁርጠኛ ነን።

በመጀመሪያዎቹ የትምህርት ጥቂት ሳምንታት ውስጥ ተማሪዎች እና መምህራን ከርቀት ትምህርት ጋር እስኪላመዱ ድረስ የተወሰነ ጊዜ በመስጠት ድጋፋችሁን እና ትዕግስታችሁን እንጠይቃለን።

# ሲንክራኒየስ እና አሲንክራኒየስ የትምህርት ጊዜ

## ሲንክራኒየስ

ከ6-12 ክፍል ያሉ ተማሪዎች በቀን የ3 ሰዓታት ሲንክራኒየስ ትምህርት ይሰጣቸዋል። ሌሎች ትምህርቶች ሁሉ በአሲንክራኒየስ ዘዴ ይሰጣሉ።

- **ሲንክራኒየስ** ትምህርት ከአንድ አስተማሪ ጋር በቨርቹዋል የትምህርት ክፍል ውስጥ የሚካሄድ የሃሳብ ልውውጥ ያለው ሁለቱም ወገኖች የሚሳተፉበት ኦንላይን ትምህርት ነው።
- **ማይክሮሶፍት ቲምስ** ማለት ለቪድዮ ኮንፈረንስ በ APS የጸደቀ ፕላትፎርም ሲሆን፣ እርሱም ለሲንክራኒየስ ማስተማሪያነት ያገለግላል። መምህራን፣ ተማሪዎች እና ወላጆች በቲምስ አማካኝነት የሃሳብ ልውውጥ ሊያደርጉ ይችላሉ።

ሲንክራኒየስ ትምህርት በታተመው የጊዜ ሰሌዳ በብሎኩ መጀመሪያ ይጀምራል። በትምህርት ክፍለ ጊዜው ውስጥ ልዩ ልዩ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴዎች አሉ። ሲንክራኒየስ የትምህርት ጊዜ ሙሉ በሙሉ ወይም በአነስተኛ ቡድኖች አማካኝነት ቀጥታ የመምህር እና ተማሪ ግንኙነት የሚደረግበት ነው።

ተማሪዎች ለሲንክራኒየስ ትምህርት በማይገኙ ጊዜ፣ መምህራን ተማሪዎቹ በአካል ተገኝተው ከሚማሩበት ትምህርት ቤት እንደቀሩ አድርገው ይወስዱታል። ተማሪዎች ያመለጣቸው ትምህርት ካለ ያንን ለማካካስ ያመለጣቸውን ትምህርት የሚያገኙበት ስፍራ ይኖራል (ይህም ማለት ተማሪዎችን ለካንቫስ መምራት)። ተማሪዎች ያመለጣቸውን ትምህርት ከድጋፍ ጋር ያገኙ ዘንድ በቢሮ ሰዓታት በትምህርት ላይ እንዲሆኑ እንመክራለን።

### ትምህርቶችን ስለመቅዳት

መምህራን የመላውን ቡድን ሲንክራኒየስ ትምህርት (ለምሳሌ የአዲስ ይዘት ወይም አነስተኛ ትምህርት መግቢያ) የተወሰኑ ክፍሎች ይቀዳሉ፤ ቪድዮውንም ፓስወርድ ባለው ፕላትፎርም (ማለትም ካንቫስ) አማካኝነት ለተማሪዎች ያቀርባሉ። የትምህርቱ አቀዳድ የግል መረጃን በማይገልጽ መልኩ ወይም የተማሪዎች ሪከርዶች በማይገለጹበት መልኩ እንዲሆን ይደረጋል። ተማሪዎች ከትምህርት በሚቀሩ ጊዜ ወይም መረጃዎችን መከለስ በሚያስፈልጋቸው ጊዜ እንዲያገኙት በመምህራን እንዲቀመጥ ይደረጋል።

ዓመታዊ ኦንላይን ማረጋገጫ ሂደት (AOVP) በሚሞላ ጊዜ ቤተሰቦች ትምህርት በሚሰጥበት ጊዜ ልጃቸው ሪከርድ እንዳይደረግ ከዚህ አማራጭ ለመውጣት ሊመርጡ ይችላሉ። ቤተሰቦች በ AOVP የጊዜ ማዕቀፍ ከዚህ ለመውጣት ያልፈለጉ እንደሆነ፣ በጽሑፍ ለልጃቸው ትምህርት ቤት በትምህርት ጊዜ ልጃቸው እንዳይቀዳ እንደሚፈልጉ በማንኛውም ጊዜ ሊያሳውቁ ይችላሉ።

***ወላጆች ትምህርታዊ የቪድዮ ሪከርድ የሚቀዳው ተማሪዎች ለትምህርት ዓላማ ብቻ እንዲጠቀሙበት ሲሆን፣ ለሌሎች ሊጋራ አይችልም።***

## አሲንክራኒየስ

- አሲንክራኒየስ ትምህርት በልዩ ልዩ ዘዴዎች ይሰጣል። ማቴሪያሎች፣ ሥራዎች እና የቤት ሥራዎች ለተማሪዎች ተደራሽ ይደረጋሉ፤ በዚህም ስር በቪድዮ የተቀዱ ትምህርቶች፣ ኦንላይን ተግባራት ወይም ኦፍላይን ስራዎች ይካተታሉ። በተማሪዎች እና በመምህራን መካከል ያለውም የሃሳብ ልውውጥ በልዩ ልዩ ዘዴዎች ሊከናወን ይችላል (ለምሳሌ በውይይት ቦርድ፣ የቤት ሥራዎች)፤ ሆኖም ግን በቀጥታ ስርጭት አይሆንም።

- በ**አሲንክራኒየስ** ትምህርት ተማሪዎች በትምህርት መገልገያቸው ወይም ከመገልገያቸው ውጪ የሚሰራ የቤት ሥራ ሊሰጣቸው ይችላል።
- በአሲንክራኒየስ ትምህርት መምህራን ትምህርትን፣ ማረምን እና የኤክስቴንሽን ተግባራትን ይደግፋሉ። እንዲህ ባለው ድጋፍ ስር ግብረ መልስ መስጠት፣ ማብራሪያ መስጠት እና ከተማሪዎች ጋር የኢሜል መልዕክት መለዋወጥ ይካተታሉ።
- በአሲንክራኒየስ ትምህርት እንደ ሁኔታው እንዲለዋወጥ እና ከተማሪ የጊዜ ሰሌዳ ጋር በተመጣጠነ መልኩ ራሱን የሚመራ ነው፤ ይህም ሆኖ ተማሪዎች ማጠናቀቅ ያለባቸውን መጨረስ ይኖርባቸዋል።

አሲንክራኒየስ ትምህርት ከ30-45 ደቂቃ/ተማሪዎች የክፍል ትምህርታቸውን እስኪያጠናቅቁ ድረስ ይወስዳሉ። ተማሪዎች በተቻለ መጠን ከመገልገያቸው ወይም ከዲቫይሳቸው ራቅ እንዲሉ የሚሰጧቸው የቤት ሥራዎች በልዩ ልዩ ፎርም ይሆናሉ። ተማሪዎች ጽሑፎችን ፕሪንት ማድረግ አይጠበቅባቸውም።

## የቤት ሥራ

በAP፣ DE እና IB የትምህርት ክፍለ ጊዜያት ካልሆነ በቀር ለአሲንክራኒየስ የትምህርት ብሎኮች ከተመደቡ ተግባራት በተጨማሪ ሌሎች የክፍል ወይም የቤት ሥራዎች መስጠት አያስፈልግም፤ ሆኖም ግን በAP፣ DE እና IB የትምህርት ክፍለ ጊዜያት ተማሪዎች በኮሌጅ ደረጃ ትምህርት ሙሉውን ሥርዓተ ትምህርት ተደራሽ እንዲሆንላቸው ከአሲንክራኒየስ የትምህርት ክፍል ተጨማሪ ሥራ ሊያስፈልግ ይችላል።

# ከተማሪዎች የሚጠበቁ ነገሮች

ሁሉም ተማሪዎች ኃላፊነት በተመላበት መልኩ እንዲንቀሳቀሱ እና ይህንኑ በተግባር እንዲያሳዩ ይጠበቅባቸዋል፤ ተማሪዎች ሌሎችን ማክበር እና በቨርቹዋል የትምህርት ክፍል ሲሆኑ፣ በትምህርት ቤቱ በሚካሄዱ ተግባራት ውስጥ እንዲሁም ከትምህርት ሰዓታት ውጪ በየዕለቱ የራሳቸውን ሥነ ሥርዓት እንዲያስጠብቁ ይጠበቅባቸዋል።

ተማሪዎች ከዚህ የሚከተሉትን እንዲፈጽሙ ይጠበቅባቸዋል፡-

- ከትምህርት ላለመቅረት፣ በኦንላይን እንቅስቃሴዎች ለመሳተፍ እና በራሳቸው ትምህርት ላይ ለመገኘት የሚቻላቸውን ጥረት ሁሉ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።
- የተሰጣቸውን ሥራ በራሳቸው በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ማጠናቀቅ ወይም አስፈላጊ ሲሆን ከወላጆቻቸው እገዛ ማግኘት።
- የርቀት የቤት ሥራዎችን (ፈተናዎችን) በመምህራን በሚሰጣቸው መመሪያ መሠረት ማጠናቀቅ።
- የተሰጣቸውን ሥራ ከማጠናቀቅ የሚያግዳቸው ማናቸውም ሁኔታ ቢኖር (ሕመም፣ ሥራ ወይም ወንድሞች/እህቶቻቸው እንክብካቤ ማድረግ) በሚኖር ጊዜ ይህንኑ ከመምህራኖቻቸው ጋር በመነጋገር መፍታት።
- APS የተሰጣቸውን መገልገያ በጥንቃቄ መያዝ ወይም በ APS ፖሊሲ እና መመሪያ መሠረት በኦንላይን መገናኘት።

ተማሪዎች በኦንላይን ትምህርት ላይ ባሉበት ጊዜ ተማሪዎች የሚከተሉትን መፈጸም አለባቸው፡-

- ተማሪዎች በትምህርት ክፍል ውስጥ መገኘት እና በንቃት መሳተፍ።
- ወደ ትምህርት ክፍል በሚመጡ ጊዜ በአግባቡ መልበስ እና በማይክሮሶፍት ቲምስ የሚታየውን የአግባብነት ያለው የኋላ ገጽታ (ደብዛዛ ወይም ሌላ ገጽታ መምረጥ አለባቸው)።
- በማይክሮሶፍት ቲምስ ስብሰባ ጊዜ (በቀጥታ ትምህርት በሚሰጥበት ጊዜ) ካሜራቸውን በአግባቡ ስለመጠቀም በመምህራኖቻቸው በተሰጣቸው መመሪያ መሠረት መጠቀም አለባቸው። ካሜራን ለማብራት እና ለማጥፋት ተማሪዎች እና/ወይም ወላጆች/አሳዳጊዎች ከሠራተኞች ፈቃድ ይሰጣቸዋል።
- በመናገር ላይ ባልሆኑበት ጊዜ ማይክሮፎኑ ድምጽ እንዳያስተላልፍ (ሚዩት) ያደርጉታል።
- በትምህርት ክፍለ ጊዜ ጥያቄ ካላቸው በማይክሮሶፍት ቲምስ ገጽታ አማካኝነት "እጃቸውን ያነሳሉ"።
- ራሳቸውን እና ሌሎች ተማሪዎችን ከመረበሽ ይቆጠባሉ (ከበስተኋላ ቲቪ አይኖርም፣ ከቤተሰብ አባላት ጋር የሚኖራቸው የሃሳብ ልውውጥ አነስተኛ ነው፣ ወዘተ)
- በመላው ቸርሹዋል ልውውጦች ወቅት አግባብነት ያለውን ቋንቋ ይጠቀማሉ። በማናቸውም ዓይነት የሃሳብ ልውውጥ ወቅት ስድብ መሰል ወይም ተገቢ ያልሆነ አነጋገር መጠቀም አይፈቀድም (ለምሳሌ ኢሜል፣ የውይይት ቦርዶች፣ የቡድን ፕሮጀክቶች ፣ የቀረቡ የክፍል/የቤት ሥራዎች)።
- እርስ በእርስ እና ከመምህራን ጋር በአክብሮት መነጋገር። ተማሪዎች ደህንነቱ በተጠበቀ ኦንላይን ሁኔታ ውስጥ በአካል በትምህርት ቤት ውስጥ እንደተገኙ ሁሉ ራሳቸውን የመግለጽ መብት አላቸው።
- አግባብነት የሌለው ኦንላይን መልዕክት የደረሳቸው እንደሆነ ለመምህራን እና/ወይም ለትምህርት ቤቱ አስተዳደር ወዲያውኑ ማሳወቅ አለባቸው።
- በራሳቸው የካንቫስ እና ማይክሮሶፍት ቲምስ ፕሮፋይል ፎቶ ወይም ቢትሞጂ ያክላሉ።

ተማሪዎች በርቀት ትምህርት ላይ ሳሉ የሚያሳዩት ባሕርይ ሁሉንም የAPS ፖሊሲዎችን የሚያሟላ መሆን አለበት፤ በዚህ ላይ መደበኛ የAPS አሰራሮች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል። እባክዎን በAPS የመመሪያ መጽሐፍ (apsva.us/wp-content/uploads/2020/08/Handbook2020-21-distance.pdf) ያለውን ይመልከቱ።

## አማራጭ ትምህርቶች (ጤና እና የአካል ብቃት ትምህርት፣ ስዕል እና CTE)

### የጤና እና የአካል ብቃት ትምህርት (PE)

ተማሪዎች ከዚህ የሚከተሉትን ይፈጽማሉ፡-

- ሲንክራኒየስ እና አሲንክራኒየስ ሞዴሎችን በመጠቀም አዲስ ይዘት ይማራሉ
- ሲንክራኒየስ እና ኢንክራኒየስ ሞዴሎችን በመጠቀም አዳዲስ ይዘትን መማር፤
- ግንኙነትን ለመመስረት በሚያስችሉ ተግባራት ላይ መሳተፍ
- አካላዊ ክህሎት የማጎልበት ሥራ መስራት/ይህንኑ ማሳየት
- በሚሳተፉበት ደረጃ ለራሳቸው የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረግ፤
- ጤናማ ውሳኔዎችን ለመወሰን የጤና ክህሎትን መረዳት እና መተግበር፤
- ወጤታማ ተግባቦት፣ ጭንቀትን መቋቋም፣ ማኅበራዊ የሥሜት ትምህርት መማር እና ግንኙነትን የመመስረት ስትራቴጂዎችን መማር፤

### ስዕል፣ ጠቅላላ ሙዚቃ እና የመሣሪያ ሙዚቃ

- ተማሪዎች ሲንክራኒየስ እና አሲንክራኒየስ ሞዴሎች በመጠቀም አዲስ ይዘት ይማራሉ።
- በቪዥዋል ስዕል ጽንሰ ሃሳቦች እና ትምህርቶች፣ በሙዚቃ መሠረታዊ ትምህርት በኖታ እና ሪትም ንባብ ላይ ትኩረት በማድረግ ተማሪዎች ካንቫስ እና ሲሳው እንዲሁም ሌሎችን ፕላትፎርሞች ይጠቀማሉ።
- ፍሊፕቦርድ፣ ተማሪዎች ከክፍል ጓደኞቻቸው እና መምህራን ጋር ከአሲንክራኒየስ እና ሲንክራኒየስ የትምህርት ሞዴሎች መካከል በመቀያየር ማኅበራዊ እና የሥነ ልቦና ግንኙነት ለመመስረት እርስ በእርስ በቪድዮ አማካኝነት እንዲገናኙ ዕድል ይሰጣቸዋል።
- እያንዳንዱ ኢንስትሩመንታል ተማሪ ኢንተራክቲቭ የኦንላይን ዘዴ መጽሐፍ እንዲያገኝ ይደረጋል፤ ይህም ተማሪዎች ቪድዮ እና ኦዲዮ ሪከርድ እንዲያደርጉ ያስችላቸዋል። በዚህም መልኩ ከመምህራኖቻቸው ጋር ፈጣን ግብረ-መልስ እና ግላዊ ግብረ-መልስ ለማግኘት ያስችላቸዋል።
- መሣሪያዎች በትምህርት ቤቱ ሳይቶች እንዲከፋፈሉ ይደረጋል።

ተማሪዎች በርቀት ሊማሩ የሚችሉ ቢሆንም፣ በአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ለሙዚቃ ያለን የጋራ ፍቅር እና የማወቅ ፍላጎት እንደ ማኅበረሰብ አንድ አድርጎ ያቆየናል።

### የሙያ እና የቴክኒክ ትምህርት (CTE)

ሁሉም በአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚሰጡ የሙያ እና የቴክኒክ ትምህርት (CTE) ትምህርቶች እና ሌሎች ፕሮግራሞች እና በ2020-21 የፕሮግራም ጥናት መሠረት ይሰጣሉ። በሁሉም

የርቀት ትምህርቶች በሙሉ ሰዓት ፕሮግራም የተመደቡ ተማሪዎች (አካዳሚክ አካዳሚ፣ አርሊንግተን ቴክ፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ተቋም እና PEP) እንዲሁም በአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ሌሎች ፕሮግራሞች የ CTE ትምህርቶች ይወስዳሉ፤ ይህን ፕሮግራም የሚሰጡት የከሪር ሴንተር መምህራን ነው።

ሁሉም የቴክኒክ ትምህርት (CTE) ተማሪዎች በሁሉም የ CTE ማዕከላት በክላስተር በሲንክራኒየስ እና አሲንክራኒየስ ሞዴሎች አዲስ ይዘት ያለው ትምህርት ይማራሉ።

- ተማሪዎች ከ CTE ብቃቶች ጋር የተጣጣሙ ትምህርቶች ይማራሉ።
- የማስተማር ሥራን ለመምራት በማለት ፎርማቲቭ ምዘናዎች በየዕለቱ ይካሄዳሉ።
- ተማሪዎች በይዘት ላይ ትኩረት ያደረገ የላብራቶሪ ሥራ ላይ ይሳተፋሉ።
- የሥራ ቦታ የክህሎቶች ዝግጅት በቨርቹዋል የትምህርት ሞዴል ይካሄዳል።
- CTE ልዩ ዘዴዎች ኪቶች፣ የፍጆታ ዕቃዎች እና የሚያስፈልጉ መገልገያዎች ይቀርባሉ።
- የርቀት ትምህርት ልምድን ለማጠናከር በአንዳንድ የትምህርት ዓይነቶች ቨርቹዋል ዘዴዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ፤
- በዚህ የትምህርት ዘመን በርቀት ትምህርት እና በተፈቀዱ የፈተና ሳይቶች አንዳንድ የፈቃድ አሰጣጥ ዕድሎች ይኖራሉ።

የ CTE ጽ/ቤት እና መምህራን ለሁሉም APS ተማሪዎች ጥራቱ የተጠበቀ እና አሳታፊ የርቀት ትምህርት ያቀርባሉ።

## የማኅበራዊ-የሥሜት ትምህርት (SEL) እና ድጋፍ

በርካታ ተማሪዎች በዚህ ወረርሽኝ ወቅት የተወሰነ ሰቆቃ መሰል ሁኔታ እንዳሳለፉ እናውቃለን፤ አሁንም ጭንቀት እና አሉታዊ የልጅነት ዘመን እያሳለፉ እንደሚሆኑም እንገነዘባለን። በዚህ ከዚህ ቀደም አጋጥሞ በማያውቅ ሁኔታ በአዲሱ የትምህርት ዘመን ተማሪዎች ወደ አዲስ የትምህርት ሁኔታ እንዲሸጋገሩ ለማድረግ፣ የተማሪዎችን አካላዊ እና አእምሯዊ ጤና ፍላጎቶች ለማሟላት በቂ ጊዜ መስጠት አለብን። የማኅበራዊ-የሥሜት ትምህርት (SEL) ለትምህርት ወሳኝ መሠረት ሲሆን፣ በመላው የትምህር ዘመን በሳምንታዊ ክፍለ ጊዜያት ውስጥ እንዲካተቱ ይደረጋል።

ከ6-12ኛ ክፍል የSEL ትምህርቶች በየሳምንቱ 30 ደቂቃ ነው።

**ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፡-** ሁሉም በሰኞ ቀናት ሲንክራኒየስ ቨርቹዋል ዘዴ የሚገለጹ ማስታወቂያዎች በሁለተኛ ደረጃ መሠረታዊ SEL ፕሮግራም አማካኝነት አስቀድሞ በቪድዮ የተቀዱ ትምህርቶችን ክለሳ እና በእነርሱ ላይ ያሉ አስተያየቶችን ያካተተ ይሆናል።

**መካከለኛ ትምህርት ቤት**:- በሰኞ ቀናት፣ አስቀድመው የተቀዱ የ SEL ትምህርቶች በመምህራን ለተማሪዎች ይመደባሉ። ሆምሊንክስ፣ ማለትም ቤተሰብዎ በቤት ውስጥ ሊያከናውነው የሚችል ተግባር ትምህርቶችን ለመለማመድ እና ለማጠንከር እንዲናገሩ ይደረጋል።

ሠራተኞች በመምህራን አድቫይዘሪ (TA) ወቅት የተማሪዎችን የማኅበራዊ እና የስሜት ደህንነት ይከታተላሉ። ይህም በየሳምንቱ የሚካሄድ ይሆናል። እንዲሁም በካንቫስ አማካኝነት በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆኑ ለማድረግ ሌሎች አስፈላጊ ከአእምሮ ጤና ጋር ተያያዥ የሆኑ መረጃዎች ለተማሪዎች ይቀርባሉ።

ተጨማሪ ሲንክራኒየስ ትምህርቶች በመረጃ መስጫ ጊዜ እና ቀደም ተብለው በተያዙ ክፍለ ጊዜያት ይሰጣሉ፤ በዚህም ስር ተማሪዎች ራሳቸውን ከማስፈራራት ሊጠበቁ ስለሚችሉበት ሁኔታ፣ የእጅ ሱሰኝነት፣ የኮሌጅ እና የሥራ ዝግጅት እና የጊዜ ሰሌዳ ማውጣት የመሳሰሉት ይካተታሉ።

አማካሪዎች ከተማሪዎች እና ከቤተሰቦቻቸው ጋር በቀጥሮ ይገናኛሉ።

## የልዩ ትምህርት ተማሪዎች ልዩ አገልግቶች

መምህራን በትምህርት ክፍል ውስጥ ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ወይም የክፍል 504 ዕቅዶችን ይከልሳሉ፤ ስለሆነም እነዚህ ፕሮግራሞች በርቀት ትምህርት ሞዴል ውስጥ ተፈጻሚ ሊሆኑ የሚችሉባቸውን ዘዴዎች ይፈልጋሉ። የልዩ ትምህርት መምህራን እና የኬዝ ካሪርስ ድጋፎች በሚገባ የታቀዱ እና ተግባራዊ መደረጋቸውንም ለማረጋገጥ ከክፍል ውስጥ መምህራን እና ከትብብር ትምህርት ቡድኖች (CLT) ጋር በኅብረት ይሰራሉ።

አንዳንድ በቨርቹዋል ትምህርት ውስጥ የተለመዱ አገልግሎቶች ከዚህ የሚከተሉትን ያካትታሉ:-

- በጽሑፍ ማቴሪያሎች እና በድምጽ ቅጂ አማካኝነት ትምህርትን ማጠናከር።
- የሁሉንም ኖቶች እና የንባብ ጽሑፎችን ቅጂዎችን መስጠት
- ተማሪዎች የይዘትን ፍጥነት ቀነስ እንዲያደርጉ መፍቀድ እና ሰፋ ያለ ጊዜ መስጠት
- ተማሪው/ዋ ስኬታማ ለመሆን በሚያስችል መንገድ ፈተና መስጠት
- ተማሪዎች አማራጭ የቤት ሥራ ዘዴዎችን እንዲጠቀሙ መፍቀድ
- የትምህርት ይዘት በልዩ ልዩ ዘዴዎች ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ
- ተማሪዎች አማራጭ የክፍል/የቤት ሥራ አማራጮችን እንዲጠቀሙ ዕድል መስጠት
- የትምህርቱን ይዘት ለመገምገም ልዩ ልዩ ዘዴዎችን መስጠት እና ተማሪዎች ሥራዎቻቸውን እና የተሰጧቸውን ሥራዎች እንዲያጠናቅቁ አማራጮች መስጠት

ከ IEP ቡድኖች ጋር ስለመተባበር ተጨማሪ ምክሮች ለማግኘት፣ እባክዎን የልዩ ትምህርት ድጋፍ እና አገልግሎቶች: ጸደይ፣ 2020 የቤተሰብ መመሪያ (*apsva.us/special-education/fall-2020-special-education-information-for-families-8-25-20/*) ይመልከቱ።

## ልዩ አገልግሎቶች ለእንግሊዝኛ ተማሪዎች

የሁለተኛ ደረጃ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች (EL) በርቀት ትምህርት አማካኝነት የእንግሊዝኛ ቋንቋ ዕድገት (ELD) ትምህርት ይሰጣቸዋል። በዚህም ስር የሲንክራኒየስ ትምህርት ልዩ ጊዜን የሚያካትት ሲሆን፣ ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ዕድገት እና ይዘትን ለማሳካት ትኩረት ይሰጣል። በተጨማሪም፣ ተማሪዎች አዲስ ክህሎቶቻቸውን ተግባራዊ እንዲያደርጉ እና በአዲስ ይዘት ላይ እንዲሰሩ አሲንክራኒየስ ጊዜ ይኖራል። የእንግሊዝኛ ቋንቋ (EL) መምህራን ሁሉንም ቡድን፣ አነስተኛ ቡድን እና እንዲያውም በርቀት ትምህርት ሞዴል ውስጥ ባሉበት ጊዜ ከተማሪዎች ጋር የተወሰነ የግል ሥራን ያካተተ ነው። የእንግሊዝኛ ቋንቋ (EL) ትኩረት በተማሪው አራት የቋንቋ ክህሎቶች ዙሪያ ይሆናል፤ እነርሱም ማንበብ፣ መጻፍ፣ መናገር እና ማዳመጥ ናቸው፤ እንዲሁም የተለየ የትምህርት ክፍል ይዘት (ለምሳሌ የእንግሊዝኛ ቋንቋ፣ ስዕል፣ ሳይንስ፣ ማኅበራዊ ጥናት፣ ወዘተ)። የሁለተኛ ደረጃ መምህራን በቅድመ አገልግሎት ሥልጠና ወቅት በርቀት ትምህርት ላይ ስለ ምርጥ ተሞክሮዎች በተለይ ደግሞ ስለ እንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ሥልጠና ተሰጥቷቸዋል።

- አግባብነት ላለው የቋንቋ እና ይዘት ግቦች ትምህርት አሰጣጥ ሲንክራኒየስ ጊዜ ጥቅም ላይ ይውላል። ይህም ተማሪዎች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ክህሎቶቻቸውን በመጠቀም ለመለማመድ ጊዜ እንዲያገኙ ይረዳቸዋል።
- በሁለተኛ ደረጃ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች የርቀት ትምህርት ሞዴሎች፡-
    - የርቀት ትምህርት የእንግሊዝኛ ቋንቋን ማጎልበት፡- የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች እውቅና ባላቸው መምህራን ይማራሉ። ትምህርቱ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ዕድገት እና በይዘት (ለምሳሌ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥበብ፣ ሳይንስ ወዘተ) ላይ ትኩረት ያደርጋል።
    - የርቀት ትምህርት በጋራ የሚሰጥ የትምህርት ክፍል - የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች በአጠቃይ የርቀት ትምህርት ሁኔታ ውስጥ ሆነው የይዘት መምህር/ት እና የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህር ይመደብላቸዋል። የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች መምህር/ት በእንግሊዝኛ ቋንቋ ላይ ትምህረት ሲያደርጉ፣ የይዘት መምህር ደግሞ በሚያስተምሩት ትምህርት ይዘት ላይ ትኩረት ያደርጋሉ።

- ሁሉም መምህራን የትምህርት ትኩረታቸውን በይዘት እና በቋንቋ ዕድገት ላይ ትኩረት በማድረግ ይዘትን እና የትምህርት ዓላማዎችን ይጠቀማሉ።
- የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ የእንግሊዝኛ ቋንቋን የማኅበራዊ የሥነ ልቦና ደህንነትን ይደግፋሉ። ስቃይ ወይም ከአዲስ ባሕል ጋር የመለመድ ችግር፣ ተመልሶ ከመቀላቀል ጋር የተያያዘ ወይም ሌሎች ችግሮች አጋጥመዋቸው፣ በእነዚህም ምክንያት በእነርሱ እና በትምህርታዊ እንቅስቃሴያቸው ላይ ተጽዕኖ ከደረሰባቸው  የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ጋር አብረው በመሥራት ላይ ናቸው።

## በባለ ልዩ ችሎታ ተማሪዎች የሚሰጡ ልዩ አገልግሎቶች

ልዩ ችሎታ ላላቸው ተማሪዎች የ APS የልዩ ትምህርት አሰጣጥ ሞዴል “ኮላበሬቲቭ ክላስተር” በመባል ይታወቃል፤ ይህም እኛ ባዘጋጀነው ዕቅድ የሚመራ ነው። ለየት ያለውን ትምህርት በማቀድ እና በማቅረብ ረገድ ይበልጥ ውጤታማ ለመሆን ልዩ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል እንዲለዩ ተደርጓል፤ በየሳምንቱም ሪሶርስ ቲቸር ፎር ዘ ጊፍትድ (RTG) ትምህርት እና ድጋፍ ይሰጣሉ። ይህም በመላው ቀን በትምህርት ቤት የዕድሜ እኩያ ላላቸው ተማሪዎች ድጋፍ ለመስጠት ቀጣይነት ያለው ዕድል ይሰጣል።

መምህራን፣ የተጠናከረ/AP/IB መምህራን እና የባለ ልዩ ችሎታ ተማሪዎች መምህራን ልዩ የግንዛቤ እና የባለ ልዩ ችሎታ ተማሪዎችን የማኅበራዊ ሥነ ልቦና ፍላጎቶች ለማሟላት ይህን ሊደግፍ የሚችል ጥልቅ አስተሳሰብን ያስተባብራሉ እንዲሁም ያቅዳሉ።

የባለ ልዩ ችሎታ ተማሪዎች መምህራን በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለክላስተር መምህራን ቀጣይነት ያለው ድጋፍ እና ምሪት ይሰጣሉ፤ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደግሞ ለተጠናከረ/AP/IB መምህራን ድጋፍ እና ሥልጠና ይሰጣል። የአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶችን ጥልቅ እና ፈጠራ የተሞላበት የአስተሳሰብ ማዕቀፍ እና/ወይም በይዘት ጽ/ቤት በሚደገፈው መሠረት ለባለ ልዩ ችሎታ ተማሪዎች በጻፈው የሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ ላይ በመመሥረት የትምህርት አሰጣጥ ዕቅድ አወጣጥን ይደግፋሉ።

የባለ ልዩ ችሎታ ተማሪዎች መምህራን ዕቅድ አወጣጥ እና ድጋፍ ለመስጠት ከልዩ ትምህርት ኬዝ ኬሪየርስ እና መምህራን ጋር በአንድነት በመሆን መተባበራቸውን ይቀጥሉበታል፤ እንዲሁም APS ክሪቲካል እና ክርኤቲቭ አስተሳሰብ ማዕቀፍ እና/ወይም በትምህርት ይዘት ኃላፊዎች በሚፈቀደው መሠረት ለባለ ልዩ ችሎታ ተማሪዎች በተጻፉ የትምህርት ጽሑፎች የሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ የትምህርት ዕቅድ አወጣጥን ይደግፋሉ።

RTG ከልዩ ትምህርት ኬዝ ኬሪየርስ እና መምህራን ጋር በቀጣይነት በመተባበር በዚህ ሰነድ ውስጥ ያለውን ኢንስትራክሽናል ኤክስፔክቴሽን በሚደግፍ መልኩ ለባለ እጥፍ ልዩ ችሎታ (2e) ተማሪዎች ዕቅድ ያወጣሉ፣ ድጋፍ ይሰጣሉ። የሚቻል ከሆነ RTG የ IEP እና 504 ሂደት አካል ይሆናል።

RTG ከፍ ያለ አእምሯዊ ብቃት ላላቸው/ባለ ልዩ ችሎታ ተማሪዎች እና የኤክስቴንሽን ተግባራት ለሚያስፈልጋቸው ድጋፍ ለመስጠት ከእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህራን ጋር መተባበራቸውን ይቀጥሉበታል።

# ከትምህርት ቤት ሰዓት በኋላ የሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች እና ስፖርት

እባካች ሁ ይህንን የወላጆች አካዳሚ ቪድዮ የወላጆች አካዳሚ ቪድዮ (youtube.com/watch?v=4s2qyclPAbo) ይመልከቱ፤ ይህ ቪድዮ ስለ ክለቦች የሥራ ተግባራት እና አትሌቲክስ በርቀት ትምህርት ሞዴል ውስጥ መረጃ የሚሰጥ ነው። ቪድዮዎች የበለጠ መረጃ ሲገኝ ወቅታዊ እንዲሆኑ ይደረጋል ።

በኮቪድ መመሪያ ስር ስንሆን፣ አርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የሥራ ተግባራቱን እና አትሌቲክስ በገዢው መመሪያ ስር የቨርጂኒያ የትምህርት ክፍል እና በቨርጂኒያ የጤና ሂደቶች ክፍል ሥር ያቀናጃል።

## አትሌቲክስ

### የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አትሌቲክስ

የአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች በዚህ ባለፈው ክረምት በከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ በሁሉም ሦስት አጠቃይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የክረምት ስፖርቶች ስኬታማ በሆነ መልኩ ፈጽመዋል። በኦገስት 21 ፣ እነዚህ የሁኔታ ክፍለ ጊዜያት ለት/ቤት የመጀመሪያ ወር የቆሙ ሲሆኑ፣ የእኛ ተማሪ አትሌቶች መጀመሪያ ተማሪ የሆኑ ለቨርቹዋል አካዳሚት ትምህርታቸው ስኬታማ ጅማሬ ማግኘት ይችላሉ። ተማሪ አትሌቶች በትምህርታቸው ላይ ሲያተኩሩ በተጨማሪም በአሰልጣኞቻቸው በቤታቸው ውስጥ ልምምዶች በመሳተፍ እንዲቀጥሉ ማድረግ ይቻላል።

የአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ለሁሉም ስፖርቶች በኦክቶበር መጀመሪያ የልምምድ ክፍለ ጊዜያትን ለመቀጠል እና ለተማሪ አትሌቶች የአካል ብቃት ሥልጠና ለመስጠት ለመቀጠል ተስፋ የሚያደርግ ሲሆን፣ በጣም የሚፈለገው ማኅበራዊ እና የስሜት ድጋፍ ለእኛ ተማሪ አትሌቶች ከአሰልጣኞቻቸው እና ሌሎች የሚታመኑ አዋቂዎች ጋር ግንኙነት በማድረግ ተፈጻሚ ይሆናል። ይህንን ክረምት ስኬት ለማብዛት እና የደህንነት ጥንቃቄዎችን ሁሉም ልምምዶች በውጪ ይደረጋሉ።

በዚህ ወቅት ተማሪ አትሌቶች በርቀት ትምህርት ሞዴል መቆየት ለመረጡ ውሳኔ አልተሰጠም ሽግግሩ እንደተፈጸመ ማለትም ሃይብሪድ/በግል ትምህርት ላይ ያሉ በግል አትሌቲክስ እና እንቅስቃሴዎች ላይ መሳተፍ ይችላሉ።

### የመካከለኛ ትምህርት ቤት አትሌቲክስ

በዚሀ ወቅት የመካከለኛ ት/ቤት አትሌቲክስ የለም። በዚህ ክረምት ጨመረሻ ላይ የበለጠ መረጃ ይሰጣል።

## ክለቦች እና እንቅስቃሴዎች

የአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ለሁሉም ተማሪዎች በቨርቹዋል መንገድ የተዘጋጁ በርካታ ክለቦች እና እንቅስቃሴዎች አሉት። የክለብ አካል መሆን ከክፍል ውጪ ጠንካራ እና ቀጣይ ግንኙነቶችን ለማስቀጠል ተመራጭ መንገድ ሲሆን፣ የአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ለተማሪዎች በርካታ የተለያዩ አማራጮች እንደ ተማሪዎች መንግሥት፣ ኦዲሴይ ኦፍ ዘ ማይንድ፣ ይርቡክ፣ ምርጥ ጓደኞች፣ ቦርድ ጨዋታዎች፣ ክርክር፣ ቴክኖሎጂ እና ሌሎችንም ያቀርባል። እነዚህ መልካም አጋጣሚዎች ለተማሪዎች ከአካዳሚ ጥናቶቻቸው ውጪ ያላቸውን ፍላጎት ለመፈጸም ችሎታን ይሰጣሉ።

ወላጆች የልጆቻቸውን የትምህርት ቤት ድረ ገጽ ስለ ክለብ ዓይነቶች እና ስለመግለጫዎቻቸው መረጃ ለማግኘት መጠቀም ይችላሉ። ድረ ገጽ እነዚህ ክለቦች በቪርቹዋል መንገድ የሚገናኙበትን እና የስፖንሰሮች የግንኙነት መረጃ ቀን እና ሰዓት መያዝ ይኖርባቸዋል።

# በትምህርት ቤት መገኘት

የቨርጂኒያ የትምህርት ክፍል (VDOE) በየቀኑ ተማሪዎች በትምህርት መገኘታቸው እንዲያዝ ያዛል። በአቴንዳንስ ላይ መኖራቸው እንዲቆጠርላቸው ተማሪዎች በየቀኑ ከአስተማሪዎቻቸው ትርጉም ላላቸው ግንኙነቶች መፈጸም እና ምላሽ መስጠት ይጠበቅባቸዋል።

አቴንዳንስ የክፍል/የቤት ሥራ ማጠናቀቅ ላይ የተመሠረተ አይደለም። አቴንዳንስ ወይም በትምህርት ክፍለ ጊዜ መገኘት  በሲነርጂ እንዲቀመጥ ያደርጋል። ቤተሰቦች በዚያው ቀን መገኘታቸውን ማረጋገጥ እና ከቀሩ ይገለጽላቸዋል።

### የዕለት ተዕለት በትምህርት ገበያ መገኘት

ከሰኞ እስከ ዓርብ የዕለት ተዕለት አቴንዳንስ ይሞላል

- ተማሪዎች "ለክፍላቸው/TA ጊዜ" ኮርስ በየዕለቱ ከሰኞ እስከ ዓርብ 4፡00 p.m. ላይ መገኘት አለባቸው።
- ይህም ለአጠቃላይ ቀኑ እንደተገኙ ያስቆጥርላቸዋል።  ይህ ካልተሞላ ግን ተማሪዎች እንደቀሩ ይቆጠራል ።
- የኢንተርኔት ኮኔክቲቪቲ ጉዳዮች ሪፖርት ማድረግ ካስፈለገ ለትምህርት ቤታቸው ሆትላይን ከ11፡00 a.m. በፊት ሪፖርት ማድረግ አለባቸው።
- ተማሪ ከታመመ እና ቼክ ኢን መሙላት ካልተቻለ ወላጆች አባካችሁ መቅረቱን ሪፖርት ለማድረግ ለአቴንዳንስ ጽ/ቤት ኢሜል እና/ወይም የስልክ ጥሪ አድርጉ።
- የአቴንዳንስ የስልክ ጥሪ በ7፡00 pm አይኖርም።

### የአቴንዳንስ ወቅት

የአቴንዳንስ ወቅት በሲነርጂ ይያያዛል። አስተማሪዎች የአቴንዳንስ ወቅት ለመቆጣጠር ማንኛቸውንም የሚከተሉትን ዘዴዎች መጠቀም ይችላሉ፡-

- ኦንላይን ቅጽ፣ ጥያቄ፣ ሰርቬይ (ማለትም፡- መውጫ ቲኬት፣ SEL ቪድዮ ጥያቄ፣ ወዘተ)
- በቻት መሳተፍ (በቀጥታ ከመምህር ጋር ወይም በአስተማሪ በተመቻቸ የግሩፕ ቻት አካል መሆን)
- ከመምህር ለተማሪ የሚደረግ የስልክ ጥሪ (በተለይ የኮኔክሽን ጋር የተያያዘ ችግር ላጋጠማቸው ተማሪዎች)
- ከክፍሉ ጋር በተያያዘ MS ቲም ሰብሰባ ተሳትፎ

ተቀባይነት ስላለው ከትምህርት መቅረት እና ስለ አቴንዳንስ ሥነ ሥርዓት መረጃ ለማግኘት የAPS የመመርያ መጽሐፍ ይመልከቱ (*apsva.us/wp-content/uploads/2020/08/Handbook2020-21-distance.pdf*)።

## ምዘና እና ውጤት

መምህራን ሴፕቴምበር ላይ በመርጣሪ እና መደበኛ በሆነ መልኩ የተማሪዎችን ዝግጁነት ይመዝናሉ። በመላው ዓመቱም ሂደቶችን ለመቆጣጠር እና የተማሪዎችን ደረጃ እና ክህሎት ያለበትን ደረጃ ለመለየት የተለያዩ ምዘናዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ። ዲጂታል የምዘና መሣሪያዎች (ማለትም ካንቫስ ኩዊዝስ) የትምህርትን ቀጣይነት ለመገምገም ጥቅም ላይ ይውላል። የተሰበሰበው መረጃም ትዕዛዞች ለመለወጥ እንዲያግዝ እና የተማሪዎችን የትምህርት ሂደት ለመደገፍ ጥቅም ላይ ይውላል።

አጠቃላይ ምዘናዎች (ለምሳሌ ፕሮጀክቶች፣ ፈተናዎች፣ ኤሴዮች) በአንድ ክፍል መጨረሻ የተማሪዎችን የብቃት ደረጃ ለመለካት ያስችላል።

ተማሪዎች ባላቸው የትምህርት ጊዜ ሲለበስ መረጃ አስተማሪዎች ከተማሪዎቻቸው ስለሚጠብቁት እና እንዴት እንደሚገመግሙ ያሳውቃሉ። ተማሪዎች በቁልፍ የመማር ደረጃዎች እና የትዕዛዝ አላማዎች ውጤት ላይ ሲበቁ ስለሚኖር ጊዜ እና ትርጉም ያለው ምላሽ ይሰጣቸዋል።

አስተማሪዎች የደረጃ ማውጣት ሂደቶች እና መመሪያዎች በትምህርት ቤት የቦርድ ፖሊሲ ትግበራ ላይ ያሉ ሥነ ሥርዓቶች I-7.2.3.34 PIP-2: ተግባበት - የትምህርት ክፍል ደረጃ ለወላጆች ሪፖርት ማድረግ (የክፍል ደረጃዎች 6-12) ይመልከቱ።

## የቴክኖሎጂ ድጋፍ

ሁሉም የመካከለኛ ደረጃ ተማሪዎች አይፓድ የሚቀበሉ ሲሆን፣ ሁሉም የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ማክቡክ ኤር ይቀበላሉ። እቤታቸው የኢንተርኔት ግንኙነት የሌላቸው ተማሪዎች የሚቀርብላቸው ሲሆን፣ ይህም MiFi ሞባይል ሆትስፖት ወይም APS አጋርነት ከኮምካስት ጋር በመተባበር ይቀርብላቸዋል። (የበለጠ መረጃ እነዚህ ላይ ይገኛል፡- *apsva.us/internet-service/*)። ሁሉም መሣሪያዎች በት/ቤታችሁ ይከፋፈላሉ።

ተማሪዎች ስለ መሣሪያቸው ወይም የኢንተርኔት ግንኙነት ያጋጠሟቸው ችግሮች ካሉ፡-

- ተማሪዎች ለመለጣቸው ለየትኛውም ክፍል/ይዘት ለመምህራን ኢሜል በማድረግ ወይም በማነጋገር (የሚችል ከሆነ)
- የትምህርት ቤት ድረ ገጻቸውን ለቴክኖሎጂ እገዛ ማሳወቅ እና ከት/ቤታቸው የትምህርት ቴክኖሎጂ አስተባባሪ (ITC) መረጃ መጠየቅ፤
- ከተቻለ እነዚህን ምንጮች በመጠቀም ችግሩን መፍታት
    - የት/ቤቱ ድረ ገጽ

- APS የርቀት ትምህርት ድረ ገጽ (*apsva.us/school-year-2020-21/technical-support/*)
- አይፓድ መገልገያዎች (*apsva.us/ms-student-technology-tutorials/*)

- የት/ቤቱ የቴክኖሎጂ እገዛ ቅጽን በመጠቀም ያጋጠሙ ችግሮችን ማቅረብ የት/ቤቱ የቴክኖሎጂ ድጋፍ (*apsva.us/digital-learning/contact-itc/*)

## የወላጆች አካዳሚ

የአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ስለርቀት ትምህርት የአርሊንግተን የሕዘብ ትምህርት ቤቶች የወላጆች አካዳሚ መረጃዎች እና የመረጃ ምንጮችን በመጠቀም ለቤተሰቦች መረጃ ይሰጣል። APS Parent Academy (*parentacademy.apsva.us*). የወላጅ አካዳሚ የተለያዩ ቀደም ብለው ሪከርድ የተደረጉ ኮርሶች፣ የቪድዮ ቱቶሪያሎች እና ተጨማሪ ኃብቶች ወይም ግልጋሎቶች የርቀት ትምህርት ሂደትን እንድትረዱ ለማገዝ እና የተማሪዎችን ልምድ ከፍ ለማድረግ ለማገዝ ያቀርባል። ለአርሊንግተን አስተማሪዎች ስለርቀት ትምህርት እና በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎችን ለመፍታት መረጃ ለመስጠት ያሉ ቪድዮዎች እና ኃብቶች እንደ፡-

- የእርስዎን ተማሪ ለመደገፍ የሚሰጥ መረጃ እና ስኬታማነት ያለው የትምህርት ከባቢ በቤት ውስጥ በማይክሮሶፍት ቲሞች ለማቅረብ የተዘጋጁ
- ቲሞችን፣ ካንቫስ፣ ሲሳው የማግኘት እና መጠቀም መንገድ
- ለሥራ እና የቴክኒክ ትምህርት (CTE) የአስተማመር ዘዴ እና የሥዕል ምርጫዎች
- የተለዩ አገልግሎቶች አቅርቦት እና የአካል ጉድለት ያለባቸውን ተማሪዎች፣ እንግሊዝኛ ተማሪዎች፣ ልዩ ሥጦታ ያላቸው ተማሪዎች ድጋፍ
- ከሥርዓተ ትምህርት ውጪ ያሉ እንቅስቃሴዎች እና አትሌቲክስ ምን መጠበቅ እንዳለበት
- ስለ ተራቀቀ ምደባ መረጃ (AP)፣ ዓለም ዓቀፍ ባካሎሬት (IB) እና ዱዋል ኢንሮልበት የምዝገባ ኮርሶች እንደ ርቀት ትምህርት ሞዴል አካል መረጃ መስጠትን ያካትታሉ፤

በመላው ዓመት አዲስ ኮርሶችን መጨመር፣ የግንኙነት ክፍሎችን ማቅረብ እና በሌሎች ፎርማቶች ሃብቶችን መጨመር ይቀጥላል።

### የእርስዎን ተማሪ መደገፍ

የእርስዎ ልጅ ለርቀት ትምህርት እንዲዘጋጅ ለማገዝ መጠቀም የሚቻሉ አንዳንድ አስተያየቶች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፡-

- የእርስዎ ልጅ የጊዜ ሰሌዳ እንዲኖረው እና እንዲከተል ማገዝ፤
- የእርስዎ ልጅ በምቾት የሚማርበትን ቦታ መለየት፣ በተለይ የእርስዎ ተማሪ መሣሪያቸውን በመጠቀም እና ሌሎችን በዴስክ ወይም ጠረጴዛ ላይ በማድረግ የሚማርበትን ቦታ ማመቻቸት
- ለአካል ብቃት እንቅስቃሴ እና ልምምድ ዕረፍት ማበረታታት፤
- የእርስዎ ልጅ መማር በካምቫስ እና/ወይም ፓረንትቪው መከታተል

- ከእርስዎ ልጅ አስተማሪ፣ የትምህርት ቤት አማካሪ ወይም አስተዳዳሪ ጋር የእርስዎ ልጅ ተጨማሪ ኃብት ወይም ድጋፍ ካስፈለገው ግንኙነት ማድረግ

## ጤና እና ደህንነት፡- ወደ ሃይብሪድ ሞዴል መሸጋገር

ጤና እና ደህንነት እንዲሁም በግል ወደመማር መሸጋገር ዋነኛው ትኩረታችን ነው፤ እንዲሁም ወደ ትምህርት ቤት የመመለስ ዕቅዳችን ዋነኛ አካል ነው። APS በ CDC፣ በቨርጂኒያ የጤና መምሪያ እና በአርሊንግተን ካውንቲ የሕዝብ ጤና ዲቪዚዮን ውጤታማ ላይ በመመስረት ውጤታማ እና አጠቃላይ የጤና እና የደህንነት ዕቅድ አለው። ተጨማሪ የጤና እና ደህንነት መረጃ በ APS ድረ ገጽ (*apsva.us/school-year-2020-21/transition-to-hybrid-in-person-model/*) ይገኛል።

APS በሃይብሪድ፣ በአካል በመገኘት በሚሰጥ ትምህርት የጤና መረጃዎች ለመከታተል እና ዕድሎችን ለመመዘን አሁንም ከክፍለ ግዛት የጤና ኃላፊዎች እና ከአርሊንግተን የሕዝብ የጤና ዲቪዚዮን ጋር አሁንም በቅርበት እየሰራ ይገኛል። ወደዚህ የትምህርት አሰጣጥ ለመሸጋገር ይቻላል ወደሚል ውሳኔ ስንደርስ በአካል ተገኝቶ ስለመማር በመጀመሪያ ለአካል ጉዳተኞች ቅድሚያ እንሰጣለን፣ ከዚያ የቅድመ መዋዕለ ሕጻናት እስከ 3ኛ ያሉ ተማሪዎች እና እንግሊዝኛ ተማሪዎች ይቀጥላሉ። በጤና መረጃ እና በጤና ኃላፊዎች በሚሰጥ መመሪያ መሠረት ወደ ሃይብሪድ በአካል ተገኝቶ መማርን ለሚመርጡ ቤተሰቦች ሁሉ ለሽግግሩ እንሰራለን።

## ቁልፍ ተወካዮች

በክፍል ሥራ/በቤት ሥራ ላይ ችግር ካለ ወይም የቴክኒክ ድጋፍ ካስፈለገ የተማሪዎን መምህር ወይም የትምህርት ቤቱን ITC ያግኙ። የልጅዎን የትምህርት ቤት ሥራ በተመለከተ እገዛ ካስፈለገዎ መጀመሪያ የሚያገኙት ሁል ጊዜም የልጅዎን መምህር ወይም ትምህርት ቤቱን ነው።

አጠቃላይ ጥያቄዎች እና ግብረ መልስ ከዚህ የሚከተለውን በመጠቀም ሊቀርቡ ይችላሉ፡- APS ኦንላይን መሳተፍ ቅጽ (*apsva.us/engage/engage-aps-online-feedback/*)።

*ለ2020-21 የትምህርት ዓመት የርቀት ትምህርት ለድጋፍዎ እና አጋርነትዎ እናመሰግናለን።*